# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 1 ቁጥር 6 ሐምሌ ፯ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.

## <u>የሁላችን፦ አንድ ነው ደማችን</u>

(የዚህን ዕትም ድምጽ ቅጂ ለማድመጥ www.ethiopiachen.org ይጫኑ)

ኢትዮጵያ፤ የሕዝቧ አንድነትና ቀራጥነት ሊመክተው ካልቻለ በቀር የወያኔ/ህወሀት የመጨረሻውን መደምደሚያ “ዕልቂት፣ ሰቆቃ፣ ዋይታ፣ ብተና፣ ግንጠላ፣ ዘር ማጥፋት፣ ሽብር፣. . .” ምዕራፍ እያነበብን ነው። ወያኔ በመግቢያው ምዕራፍ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቧ እኩልነት የቆሙትን ወገኖች እየጠራረገና እያወደመ፣ የራሱንም ወገኖች እያረደና በቦምብ እያስደበደበ ለሀገርና ለሕዝብ ሳይሆን ለዕኩይ ሰይጣናዊ ተግባሩ ቤተ መንግስቱን ከተቆጣጠረ እነሆ 26 ዓመቱ። የወያኔን ማጠቃለያ ፈንጂ ልናመክን ካልተባበርን ማዘን ያለብን በራሳችን ነው። በወያኔ ምዕራፍ አንድ የዘረኝነት ጉዞ ያነጣጠረበትንና ሊያጠቃው የተነሳውን አማራ “ወኪል የለውም” በሚል በበደኖና አርባ ጉጉ ሲያስጨፈጭፍና ሲያሳርድ ተጠናክረን ልንታገል አለመቻላችን ዛሬ አድማሱን አስፍቶ በመላው ሀገሪቷ የዘር ማጥፋት ጥይት እያጓራ ነው።

ትላንት ፓን አፍሪካኒዝም ዋና አቀንቃኝ በመሆን አፍሪካን በባህል፣ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ልታስተሳስር ቀዳሚውን ሚና ትጫወት የነበረችው ሀገራችን ዛሬ እራሷን እንደ አንድ ሀገር ለመጠበቅ ያላት አቅሟ እየተመናመነ ይታያል። ኢትዮጵያ ሀገራችን በዮዲት ጉዲትና ግራኝ መሐመድ (አህመድ) በተካሄዱባት አስከፊ ወረራ በርካታ ታሪካዊ ቅርሶቿና አብያተ ክርስቲያን ቢወድሙባትም የአቅሟን መክታ ክርስቲያኑንና እስላሙን አማኝ በአንድነት ይዛ ተጉዛለች። የድርቡሽ ወረራን ተቋቁማ፣ በዶጋሌ አሉላን ወልዳ፣ በቴዎድሮስ ደም ተንኮሎኞችን አሳፍራ የመለሰች የኢትዮጵያ መቅደላ፣ ከቅኝ ግዛት በላይ ነፃነትን ያውለበለበች የዐድዋ እመቤት ኢትዮጵያ፣ ዳግም ነፃነቷንና ክብሯን በአምስት ዓመት የአርብኝነት ተጋድሎ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማዋ ያስዋበች ሀገራችን ኢትዮጵያ እሳት ወልዳ ሲለበልባት እያየን ነው። “እንዳትተወው ልጅ ሆነባት. . .” እንዲሉ ሲፈጀት የከረመው እሳት ዛሬ ጨርሶ ሊያነዳት የመጨረሻውን ምዕራፍ እያገላበጠ ይገኛል።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከደረሰባት የተለያየ ጥቃትና መከራ የወያኔው ልዩ የሚያደርገው አምባገነንነቱ ከሀገርና ሕዝብ ጥላቻ ጋር የተቆራኘ መሆኑ ነው። አጥፊዋ የነገሰበት ዘመን፣ ገዳይዋ የተሞሸረበት ዘመን፣ ጠርንፎ የያዛት ወንበዴ ሀገር ሲያል ስትሆንበት፣ አሕዛብ አሪያስ ሲሆኑበት፣ የታየበት ዘመን ቢኖር የወያኔ/ህወሀት የአገዛዝ ዘመን ነው።

የወያኔና ሻቢያ ኢትዮጵያን የመበታተንና ሕዝቧን የማጥፋት ጣምራ ጅምር እነሆ በወያኔ መውደቅና በልጆቿ ድል አድራጊነት እንደሚጠናቀቅ ቢገመትም ጉዞው ሊታመን የማይችል ጥፋቶችን በሀገርና በሰው ልጆች ላይ እንደማያስከትል አፍን ሞልቶ መናገር አዳጋች ነው። ዛሬ በጎንደርና ጎጃም አካባቢ እየተካሄደ ያለው የጅምላ አንድ ዘር ጭፍጨፋ ለወያኔ የዕቅዱ ምዕራፍ ነውና አያሳስበውም። ለወያኔ አማራን መፍጀት አጀንዳው ነውና አይጨንቀውም። ለወያኔ ክርስትና ሃይማኖትን ከኢትዮጵያ ማጥፋት የብተናው ክፍል አንድ ነውና ሰይፉን እየሳለ ሳይሆን የሳለውን ሰይፍ ሊያሳርፍ በተጠንቀቅ

ነው። ወያኔ/ሻቢያ ለፖለቲካ የበላይነታቸው የራሳቸውን ወገኖች ያረዱ፣ ዕኩይ ተግባራቸውን አውቆ አላስጠጋ ያላቸውን ሐውዜን ላይ ያስጨፈጨፉ፣ ኢትዮጵያን አላስነካ ላላቸው ቃታቸውን የሳቡና እየሳቡ እንደሚገኙ ምስክር አያሻም።

ወያኔ/ህወሀት ለአለፉት 26 ዓመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሰሚ በሚዘገንን መልኩ እጅጉን አሰቃይተዋል፣ በየእሥር ቤቱ አጉረዋል፣ ገርፈዋል፣ ገድለዋል። በየክፍላተ ሀገሩ የተጨፈጨፉ፣ የት እንደደረሱ የማይታወቁ ወገኖቻችን ቤቱ ይቁጠራቸው። ወያኔ/ሻቢያ ከድኅረ ሥልጣን ጀምሮ፣ በትረ መንግሥቱን ከያዙበት ጊዜ አንስቶ፤ በጫካ ታሪካቸውም ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዜግነት መብት የሚታገሉ ኃይሎችን በተቀነባበረ ሤራ እያዳከሙና እያጠፉ ለመንዛቸው ታሪክ ምስክር ነው። ዛሬም በአይዞህ ባይ ባዕዳን እገዛ እነጣጥረው ያሉት ስለ ሀገርና ሕዝብ አንድነት ሰባኪዎች ላይ ነው። በተለይ ከ1997 ዓ.ም. የምርጫ ንቅናቄ ማግስት ወያኔ የሕዝቡን ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትና አንድነት ለመበጣጠስና ዘረኝነት ከፍተኛውን ሥፍራ ያገኘ ዘንድ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም የተጫወተው ሚና ዛሬ “ድል አድራጊነቱን” ያበሰረለት ይመስላል።

አንድ ዘርን ይዞ ኢትዮጵያዊነትን ማንገስ እንደማይቻል ለኦሮሞም፣ ለትግሬም፣ ለአማራም፣ ለጉራጌም፣ ለአኝዋክም፣ ለአፋርም ወዘተ. ኅሳ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ኢትዮጵያዊነት እንዲያብብ የኢትዮጵያ ዘር መተከል ሊያጠያይቅ አይገባውም። የኢትዮጵያ ችግኝ ነው የሀገርን ብሔራዊ ስሜት የሚያበቅለው፤ የሚያጎላው። “ዱባና ቅል አበቃቀሉ . . .” እንዲሉ ኢትዮጵያ ነች ኦሮሞን የወለደች፣ ኢትዮጵያ ነች አማራን የወለደች፣ ኢትዮጵያ ነች ትግሬን የወለደች፣. . .፣ ኢትዮጵያ ነች አንድ ሕዝብና የተለያዩ ነገድና ኅሳዎች የወለደች። ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያደረጓት የተለያዩ ብርቅዬ ነገድና ኅሳዎቿ ናቸው።

ከወያኔ ባሻገር ዛሬ ስለ ዘር ሰባኪዎች ትላንት ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አማራ፣ ጉራጌ… ሳይሉ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ለሀገር አንድነትና ለዴሞክራሲያ መብት ሲታገሉ የነበሩ ሆነው ማየቱ “ኧ…ረ… ወዴት እየሄድን ነው?” ያሰኛል። “ኧ…ረ… ስለ ሀገርና ሕዝብ ብለን ወያኔን ለመታገል ያለንን ኢትዮጵያዊነት ሞራላችንን አንጣል” ያሰኛል። የላላውን ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜታችንን አጠናክረን በጋራ ወያኔን መጋፈጥ ሲኖርብን ከዘርም አልፈን ጎንደሬ ከጎጃሜ ከሸዌ በየፊናው ሲጓዝ፣ ዘር በክፍለሀገር ሲሸነሸን እውን “ድል አድራጊው” ገዳያችን ወያኔ አይደለም እንዴ? ወደድንም ጠላን በክልልም ሆነ በዘር መሰባሰብ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜትን መሸርሸር ብቻ ሳይሆን፣ “ለኢትዮጵያ አሳቢ እኔ ብቻ ነኝ” የሚል ጠባብ ክልላዊ አስተሳሰብ ውስጥ ይዘፍቃልና ወያኔ በዘርና በክልል ያተራመሳትን ሀገራችንን ከከፋ አደጋ ለማዳን “ኢትዮጵያ! እንበል” ስንል “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ድምፃችንን እናሰማለን፣ ጽሁፋችንን እናስነብባለን።

በተለያየ ጊዜ የተነሱት የኦሮሞ ልጆች እንቅስቃሴዎች ከሌሎቹ ወገኖቻቸው የመብት ጥያቄ የተለዩ አይደሉም። የሙስሊሙ ኅብረተሰብ የመብት ጥያቄ በክርስቲያኑም ዘንድ አለ። የአማራውን የዴሞክራሲና የሕዝብ መንግስት ጥያቄ ሁሉም ዜጋ ያነሳዋል። ወያኔ በዘር ከፋፍሎ እየገዛና እያጠቃ ነውና የምላሹ አሰላለፍና መከላከል ዘርን ተገን ቢያደርግ አያስደንቅም። ትልቁ ጥንቃቄ “ይህ ዘር ለኢትዮጵያ የቆመ”፣ “ያኛው ሊገነጠል ያሰፈሰፈ” እያልን የአንዳንድ ፖለቲካ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ሹክቻ ሕዝቡ ውስጥ እንዳይሰርጽ መጠንቀቅ ይጠበቅብናል። ኦሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ጋምቤላው፣ አፋሩ፣ ነገ ትግሬው፣ በየአካባቢው መነሳሳቱ ጠቀሜታ ቢኖረውም ሀገራዊ ማንነቱንና የጋራ ጥያቄውን በማቀናጀት ለጋራ ችግሩ የጋራ መፍትሄው ላይ ማተኮር እንደሚገባ “ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ማስገንዘብ እንወዳለን።

ጎጃም ያረሰውን ወለጋ እንዲገዛ፣ የጎንደርን እስክስታ ጉራጌ እንዲያደምቀው፣ የትግሬን አንባሻ አማራ እንዲጋግረው፣ የኦሮሞን ቆንጆ ትግሬው እንዲያገባ፣ የጉራጌ ክትፎ ያገር ምግብ እንዲሆን፣ በወሎ እሪኩም ሐፋር ካልዘነጠ፣ የሸዋን ደበሎ ኦሮሞ ካልደረበ፣ በኦሮሞ ገዳ አማራ ካልኮራ . . . እኮ ምኑን ሀገር ስለ ሀገር ተወራ። ይህ ተዘርዝሮ የማያልቅ ውብ ባህላችን፣ ምግባችን፣ ቋንቋችን፣ ዘራችን፣ መልካችን፣ ዘፈናችን፣ የሁላችን የኢትዮጵያችን ካልሆነ ሀገር ምኑን ሀገር ሆነች? ማንነታችንስ ምኑን ኢትዮጵያዊ ሆነ? ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ስንል፣ ኢትዮጵያዊ ነን ስንል ኦሮሞም፣ ጉራጌም፣ ትግሬም፣ አማራም፣ ሁሉንም፣ ሁሉንም ማለታችን አይደል? ይህማ ካልሆነ ምኑን "ደማቸው ደማችን"፣ "ደማችን ደማቸው" አልን። የአፋር ግመል ሚቆምላትን ሰንደቅ ዓላማዋን ከፍ ስናደርግ፣ በተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎቻችን ለኢትዮጵያ ስንዘምር፣ ፉከራ ቀረርቷችን ለሀገር ክብር ስንሰጥ፣ በአንድ ማዕድ እጃችንን ስንዘረጋ፣ ለኢትዮጵያ ስለ ኢትዮጵያ ስንሰብክ አንድነታችን ይጠናከራል። አንድነታችን በሚፈጥረው ትብብራችን፣ ብሔራዊ ስሜታችን ወያኔ/ሻቢያ መሰል ጠላቶችን ለአንዴም ለመጨረሻ የመገላገያው ድል የእኛ፣ የሀገርና የሕዝብ ይሆናል። ይህን ጊዜ የዜግነት መብት የተከበረባት፣ ሁሉም ጎሳና ነገዶች እኩል ሚታዩባት፣ ፈቷን ለዕድገትና ልማት የሰጠች ኢትዮጵያ በልጆቿ ለልጆቿ ትሆናለች።

ሕዝባዊ ቁጣና ዐመጽ ሲያይል በደርግ አገዛዝም አዋጅና ቀረርቶ አንድ ትውልድ እምሽክ አድርጓል። ታሪክ አጥፊዎችን እየደጋገመች ወያኔም የሕዝብ መነሳሳትን በሕግ ላይ ሕግ በማውጣት ሀገሪቷንና ሕዝቡን በወታደራዊ ዕዝ ሰንሰለት ከተበተብ ከረምረም ብሏል። እራሱ ለሕግ ያልተገዛ አገዛዝ ስለ ሕግ ሊደሰኩር የሞራል ብቃትም የለው። ሲጀመርም የወያኔ ሕገ መንግስት ሀገር በታኝ ሕዝብ ከፋፋይ ነውና ለኢትዮጵያ ሲባል ከነሥርዓቱ መደርመስ ያለበት ነው። አፋኝ ሕገ መንግስት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንመኝምና። በታኝ ሕገ መንግሥት ለተለያዩ ጎሳና ነገዶች አይበጅምና። የወያኔ ሕገ መንግስት ሀገር መግዛት ቢያቅታቸው ትግራይን ገንጥሎ በመሸሽ ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት የተቀመመ መርዝ ነው። ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግን ማስወገድ ሲባል አንድ አምባገነን በሌላ ይተካ ማለት አይደለም። የወያኔ ሕገ መንግስት አፍኖና ረግጦ ከመግዛትም ባሻገር ሀገር ለመገነጣጠልና ለእርስ በርስ ጥላቻ የተመቻቸ በመሆኑ ለወያኔ መከፈኛ ከመሆን መዝለል የለበትም። የዚህ መርዘኛ ሕገ መንግሥት ጦስ እየተመዘዘ ዛሬ ደግሞ የአዲስ አበባን ነዋሪ ሲያተራምስ በገሃድ ይታያል።

በኦሮሞ ልጆች በኩል የተነሳውን ሕዝባዊ ቁጣ ማባበያ ይሆን ዘንድ ሰሞኑን አዲስ አበባን በተመለከተ የወጣው የዚህ መርዘኛ አገዛዝ አዋጅም ሆነ ልፈፋ የወያኔን ማንነት ከተረዳን በትንሹ ሁለት ምዕተ ዓመታት ስላስቆጠርን ሊያስደነግጠንም ሆነ ሊገርመን አይገባም። ወያኔ ካነጣጠረበትና ሊያጠፋውና ሊበታትነው ከሚፈልገው አካባቢ አንዱ አዲስ አበባ ነው። የአዲስ አበባ ነዋሪ የዚህ ዘር ነህ የማይባል፣ ክልልህ ይህ ነው ያልተባለ የሁሉንም ኢትዮጵያ ዘሮችና የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች በአርአያነት አቅፋ ያለች ናት። አዲስ አበባ እንዴት አድርጋ ሁሉንም ባህል፣ ቋንቋ፣ ምግብ፣ ሸቀጥ፣ ዘር፣ ሀብታም፣ ደሃ፣ እስላም፣ ክርስቲያን ሳትል አስተናግዳ ኢትዮጵያዊነት መቻቻል፣ አብሮ መኖር፣ አብሮ መብላት፣ አብሮ መጠጣት፣ አብሮ መጨፈር፣ አብሮ ማልቀስ፣ አብሮ መሳቅ፣. . . የተላበሰች መዲና የወያኔዎች ብቻ ትሆን ዘንድ የዕቅዱ መጀመሪያ የዛሬ 26 ዓመት የተጠነሰሰ ነው።

ወያኔ የአዲስ አበባን ነዋሪ ማስመረርና ማሰቃየት የጀመረው ሥልጣን በያዘ ማግሥት ነው። በትንሹ ለ10 ዓመት ወያኔና/ሻቢያ በጋራ አሰቃይተውታል፤ አስመርረውታል። ኤርትራያኖች እገቡበት ቡና ቤት መግባት እስኪያስደበድብ ድረስ መከራውን ያየው የአዲስ አበባ ነዋሪ ለዚህ ምስክር ነው። የሁለት ገንጣዮች ጸብ ሻቢያን ቢገላግለውም የወያኔ በትር ለአዲስ አበባ ሕዝብ በረታ እንጂ አልቀለለለትም።

ቦታው ለልማት ይፈለጋል እና በሌላም ሌላ ሰበብ መተኪያ መኖሪያ ሳይሰጠው የትም የተወረወረው ቤተሰብ ቀላል አይደለም። ልዋጭ መተኪያ ተብሎ ቢሰጥም በአካባቢው የተከፈተ ትምህርት ቤት፣ የዕለት ተለት መገበያያ ጉልት እና የመሳሰሉት ባለመኖራቸው ልጆቹ "ትምህርት ከሆድ በኋላ" በሚል ለጎዳና ተዳዳሪነት፣ ለሴተኛ አዳሪነት፣ ለወያላነት፣ ለስደት፣ እና ለመሳሰሉት የተዳረጉት ወገኖቻችን ቀላል አይደሉም።

በነጋዴዎች ላይ በየጊዜው በሚጨምረው የቤት ኪራይና ግብር ሳቢያ ንብረታቸውንና ቤታቸውን ዛሬ ወያኔዎች ሕንፃ ገንብተውበትና አስረሽ ምቺው ሲጨፍሩበት በቁጭት ዓይን ተመልካቹ ቀላል አይደለም። በየመንገዱ ጋሽዬ እ..ራ..በ..ኝ..፣ ጋሽዬ ጣ..ል አርግልኝ፣ ጀለስዬ፣ ፍሬንድዬ . . . ባዩ ለዚህ እንግልት ኑሮ የተዳረጉ የአዲስ አበባ ነዋሪ ልጆች ናቸው። የአዲስ አበባ ቆሼ ተመጋቢዎችን ስናይ እውን ወያኔ የሰው ልጅን ከውሻ አላሳነሰም? በየምግብ ቤቱ ትርፍራፊ ሊገዛ የተሰለፍው ያገኘውን በጉርሻ መልክ ሲቸረችር እውን ይህ ነው የ26 ዓመት ዕድገት?

የአዲስ አበባን ነዋሪ ቤተሰባዊና ማኀበራዊ ህይወት ለመበጣጠስ ዕድር ሚባል ከተበተነ ሰንበትበት ብሏል። በአዲስ አበባ እስላም ከክርስቲያኑ አብረው በልተው፣ አብረው ጠጥተው፣ እርስ በርስ ተፋቅረው፣ ብሎም ተጋብተው፣ ሀዘንና ደስታቸውን በጋራ ተደጋግፈው እንዳልተቀበሉ ዛሬ ዕድሜ ሳይሆን ሞት ለወያኔ እንበልና መጨባበጥና ሰላምታ መለዋወጥ አስፈሪ እሆነበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

ሰሞኑን "የኦሮሚያን ልዩ ጥቅም ማስጠበቅ" በሚል ተራ የወያኔ ማጭበርበሪያ ፈሊጥ ሕግና ሕገ መንግስቱ እየተባለ ሲላዘን "ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ ይሏታል ጂግራ" ካልሆነ በቀር ወያኔ አንዱን ዘር በሌላው ላይ ለማነሳሳት ከሚጭረው ክብሪት የተለየ አይደለም። በንግዱም ሆነ በነዋሪነት ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ወያኔዎቹ ከአላቸው ዘለቄታዊ ፍላጎት አንጻር በመብትና በሕግ ስም ከኦሮሞ ወገኖች ጋር አዲስ አበባን ለማጋጨት የሚሸርበው መርዛማ ተልዕኮ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ላይ እየተበየነ ያለው ዓመታዊ ግብር "መደብራችሁን እየዘጋችሁ ሂዱልን" እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም። የወያኔ የዕድገት ደረጃ ጥፋት ነውና መፍትሄው ልቅሶ አይደለም። ይህ አገዛዝ እንዲያበቃለት ሕዝባዊ ዐመጹን በጋራ ማፋፋም ይጠይቃል። ወያኔ ኢትዮጵያን እንደማይበትን ማሳየት ይኖርብናል። ኢትዮጵያ ማለት ኦሮሞ፣ ኦሮሞ ማለት ኢትዮጵያ መሆኑን ማሳየት ይጠበቅብናል። ኢትዮጵያ የኦሮሞን ልጆች አይደለም ወያኔ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሬዋለሁ የሚለውን የትግራይ ልጆችን እንደማያገኝ መናገር ትንቢት አይደለም።

እኛ ኢትዮጵያ ስንል ትግራይን ነጥለን አይደለምና። እኛ ኢትዮጵያ ስንል ኦሮሞ ዋርካችን ነውና። እኛ ኢትዮጵያ ስንል አማራ ሀገሩ ናትና። እኛ ኢትዮጵያ ስንል አቦ ጉራጌ እያልን ነውና። እኛ ኢትዮጵያ ስንል ግመሌን እያልን ነው። እኛ ኢትዮጵያ ስንል ለጋምቤላ ምስኪኖች እየጮህን ነውና። እኛ ኢትዮጵያ ስንል ጎሙጎፋ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ሲዳሞ፣ ኢሉባቡር፣ ከፋ፣ ወለጋ፣ ትግሬ፣ ወሎ፣ ጎንደር፣ ጎጃም፣ ሸዋ፣ አዲስ አበባ፣ ሐረርጌ፣ . . .***የኢትዮጵያ ልጆች ሁላችን. . .ሁላችን አንድ ነው ደማችን*** እያልን ነው።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

***በወያኔ የመከራ ጅራፍ እየተሰቃየህ ከሁለት ምዕተ ዓመት በላይ ተጉዞሃል። የመከራና የስቃይህ ማብቂያ "ቀጣዩ ገዥ ደግሞ ማ ይሆን?" ሳይሆን "ቀጣይ ሀገሬ ኢትዮጵያ ትሆን?" የሚለው ሆኗል። በከተማም በገጠርም ወያኔ የሰው ልጅ ከሚችለው በላይ የግፍ ዓይነቶችን ፈጽሞብሃል። የኢትዮጵያ ብርቅዬ ሰብሎች በማዳበሪያ ስምና በተዳቀሉ ባዕድ አመጣሽ ዘሮች እንዲመክኑ ተደርገዋል፣ ደኖች እየተቃጠሉና እየተመነጠሩ ለባዕዳን ባለሀብቶች ተቸብችበዋል፣ ከኖርክበት ቀዬ እየተፈናቀልህ እንደ ዕቃ ተወርውረሃል፣ ተጥለሃል። ንዋይ ናፋቂው ወያኔ በአንተና በልጆችህ ደም ሀብትህን ዘርፏል፣ ሀገር አራቁቷል። ለዜጎች ጥቃት ደንታ የሌለው ወያኔ ወንድም እህቶቻችን በየአረብ ሀገሩ እንደከብት ሲቀሉ ዝምታን መርጧል። ለነዚህና መሰል ብሶትህ በተለያየ ወቅት ያደረካቸው ሰላማዊ እቅስቃሴዎች ምላሽ እስር፣ አፈናና ግድያ ከመሆን አልፎ ገሃድ ለወጣ ወታደራዊ ግደለው፣ፍለጠው አገዛዝ በአዋጅ ደረጃ ተዳርገሃል። ወያኔ የመጨረሻ ዕልሙ ሀገሪቷን መበታተን ነውና ለዚህ ደግሞ የተራበና የተዳከመ ኅብረተሰብ አመቺው በመሆኑ ልጆችህን በረሃብ አለንጋ እየቀጣ ሀገራቸው ላይ ያማርሩ ዘንድ ጥሯል። ከዘረኝነት ወጥመድ እንዳይወጣ ልጆችህ ሀገራቸውንና ማንነታቸውን እንዳያውቁ ያደረገውና እያደረገ ያለው ያላሰለሰ ጥረት ልትመክተው የምትችለው ከረሃብና ስቃይህ በላይ መሆን በሚገባው የሀገር ፍቅር ስሜት መሆን ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ከነችግሯ፣ ከነችግራችን የሁላችንም ናትና ይህን መርዘኛ አገዛዝ ወደ ትቢያው ለመክተትና ሀገርና ሕዝብን ለማዳን ተነስ። የነፃነት መፍትሄው ቁልፉ በእጅህ ነውና በደምና አጥንትህ ኢትዮጵያን ጠብቃት። ኢትዮጵያ እንድትኖር እንሙትላት። ለልጆቻችን ሀገር፣ ፍቅር፣ ደስታ እንድናወርስ እንነሳ። እንላለን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"***

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"**
**ሐምሌ** 7 **ቀን** 2009 **ዓ.ም**. (July 14, 2017)

**የዚህን ዕትም ድምጽ ቅጂ ለማድመጥ** www.ethiopiachen.org **ይጫኑ።**

<u>ማሳሰቢያ ፡</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምስለ ገጽ : Ethiopiachen Hagerachen